በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
አሐዱ አምላክ አሜን!

# ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን

# ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን

- ምሥጢራተ ቤ/ክ ረቂቁን ማለትም የማይታየውን እና የማይዳሰሰውን የእግዚአብሔርን ጸጋ የምንቀበልባቸው መንፈሳዊ ሥርዓቶች ናቸው፡፡
- ምሥጢራት የተባሉበትም ምክንያት በዓይናችን ልናያቸው፣ በእጃችን ልንዳስሳቸው የማንችላቸው ልዩ ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በነዚህ ምሥጢራት አማካይነት የሚሰጡን ስለሆነ ነው፡፡
- በመ/ምሳሌ 9፣1-2 ‹‹ጥበብ ቤቷን ሠራች፤ ሰባቱንም ምሰሶዎቿን አቆመች›› ተብሎ በተጻፈው መሠረት የቤ/ክ ምሥጢራት በቁጥር 7 ናቸው፡፡
- እነዚህም፡- ጥምቀት፣ ቅብዓተ ሜሮን፣ ቁርባን፣ ክህነት፣ ተክሊል፣ ንስሓ፣ ቀንዲል ናቸው፡፡

# 1- ምሥጢረ ጥምቀት

- ‹‹ጥምቀት›› የሚለው ቃል ‹‹አጥመቀ›› (አጠመቀ፣ ነከረ፣ ዘፈቀ) ከሚለው የግእዝ ግስ የሚወጣ ሳቢ ዘር ሲሆን ትርጉሙም በውኃ መንከር፣ መዝፈቅ፣ ማጥመቅ ማለት ነው፡፡

- ጥምቀት ከሰባቱ ምሥ/ቤ/ክ የመጀመሪያው (በር) በመሆኑ አንድ ሰው በሥላሴ (በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ) ስም ተጠምቆ የቤ/ክ አባል ካልሆነ በስተቀር በሌሎቹ ምሥጢራት ሊሳተፍ አይችልም፡፡

## ከክርስቲያን ጥመቀት በፊት (በብሉይ ኪዳን) የነበሩ የጥምቀት ምሳሌዎች እና ዓይነቶች፡-

ሀ) በብሉይ ኪዳን የነበሩ የጥምቀት ምሳሌዎች

የኖኅ መርከብ፣ ግዝረት፣ የእሥራኤል ቀይ ባህርን መሻገር… በሐዲስ ኪዳን ለክርስቲያን ጥምቀት ምሳሌዎች ሆነው ተጠቅሰዋል፡፡

- የኖኅ መርከብ

‹‹ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፍስ በውኃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ፣ የእግዚአብሔር ትዕግስት በኖኅ ዘመን በቆየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም፡፡ ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል…›› (1ጴጥ 3፣20)

# ግዝረት

- የግዝረት ቃልኪዳን የተሰጠው ለታላቁ አባት አብርሃም ነው፡፡ ከአብርሃም ቤት/ዘር የሚወለድ ወንድ ሁሉ በ8 ቀኑ እንዲገረዝ ታዝዞአል (ዘፍ 17፥9)፡፡
- ይህም ግዝረት በእግዚአብሔር እና በአብርሃም ብሎም በዘሩ መካከል ላለው ቃልኪዳን ምልክት ነበረ፡፡
- በሐዲስ ኪዳን ግን መገረዝም ሆነ አለመገረዝ ጥቅም እንደሌለው ተነግሯል (ገላ 5፥2-6)፤ ሮሜ 2፥28-29)
- ምክንያቱም ግዝረት በጥምቀት ተተክቷል እና ነው፡-

‹‹… በክርስቶስ መገረዝ፥ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ በእርሱ ሆናችሁ ደግሞ ተገረዛችሁ፤ በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀበራችሁ፡፡ በጥምቀትም ደግሞ ከሙታን ባስነሳው በእግዚአብሔር በማመናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሳችሁ›› ቆላስይስ 2፥11-12

## የእሥራኤል ቀይ ባህርን መሻገር

- ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ በግብጽ አገር በስደት ይኖሩ የነበሩ እሥራኤላውያን በእግዚአብሔር ፈቃድ ቀይ ባህርን መሻገራቸውን ለክርስቲያን ጥምቀት ምሳሌ አድርጎ ጽፏል፡-

‹‹አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ፤ ሁሉም በባህር መካከል ተሻገሩ፤ ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመና እና በባህር ተጠመቁ…››1ቆሮ 10፡1-2

## ለ) ከክርስቲያን ጥመቀት በፊት (በብሉይ ኪዳን) የነበሩ የጥምቀት ዓይነቶች፡-

- የአይሁድ የማንጻት ጥምቀት
- የመጥምቁ ዮሐንስ የንስሓ ጥምቀት (ማቴ 3፥11፤ ማር 1፥4፤ ሉቃ 3፥3፤ ሐዋ 13፥24፤ 19፥4)
- ሐዋርያት ከጌታ ሞት እና ትንሣኤ በፊት (ጌታ ከእነርሱ ጋር በአካል እያለ) ያጠምቁት የነበረው የማዘጋጃ ጥምቀት (ዮሐ 4፥2 አነጻጽር ዮሐ 3፥22)
- የዮሐንስ እና ሐዋርያት ቀደም ሲል ያጠምቁት የነበረው ጥምቀት ሰዎች ጌታችንን እንዲቀበሉት ለማዘጋጀት የተደረገ የንስሓ ጥምቀት ነው እንጂ ልጅነትን የሚያሰጥ አልነበረም።

# የክርስቲያን ጥምቀት /ጥምቀተ ክርስትና

- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ፣ በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ በጥምቀቱ ጥምቀተ ክርስትናን መስርቶልናል (ማቴ 3፥3-17፤ ሉቃ 3፥21-22፤ ዮሐ 1፥32-34)።

- ጌታችን ‹‹ሰው ከውኃ እና ከመንፈስ ካልተወለደ (ካልተጠመቀ) በቀር ወደእግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም…›› በማለት ጥምቀት ወሳኝ (የግድ የሚያስፈልግ) መሆኑን አስተምሮናል (ዮሐ 3፥3-7፤ ማር 16፥16)።

# የክርስቲያን ጥምቀት…

- በመሆኑም በጥምቀተ ክርስትና፡-
  - የእግዚአብሔርን ልጅነት (ዳግም መወለድን) እናገኛለን፡፡ የክርስቶስ ቤ/ክ አባላት እንሆናለን (ዮሐ 3፣3-7፤ ማር 16፣16፤ ሮሜ 6.3-5…)፡፡
  - የተለያዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን (ጸጋዎችን) እንቀበላለን (ሐዋ 2፣38፤ 19፣5-6፤ 1ቆሮ 12፣4-11…)፡፡
  - የኃጢአት ሥርየትን እናገኛለን (ሐዋ 2፣32፤ 1ቆሮ 6፣11)፡፡

# በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ማጥመቅ

- የክርስቲያን ጥምቀት የሚከናወነው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ (በቅድሥት ሥላሴ) ስም ነው። ምክንያቱም

- ጌታችን በተጠመቀ ጊዜ አብ በደመና ሲመሰክር፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በርግብ አምሳል በመውረድ ምሥጢረ ሥላሴ በዮርዳኖስ (በጥምቀት) ተገልጧል (ማቴ 3፣3-17፤ ሉቃ 3፣21-22፤ ዮሐ 1፣32-34)።

- የጌታችንም ትእዛዝ ይኸው ነው። ‹‹… እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው… ደቀመዛሙርት አድርጓቸው (ማቴ 28፣19)።

# በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ...

- በሐዋርያት ሥራ (ም 2፣38፤ 8፣12፤ 10፣48፤ 19፣5...) ላይ ሐዋርያት ‹‹በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ›› ብለው እንዳስተማሩ እና በስሙ እንዳጠመቁ ተገልጾአል፡፡

- ይህም ማለት በወቅቱ ይታወቅ ከነበረው ከዮሐንስ የንስሐ ጥምቀት በተለየች እና ኢየሱስ ክርስቶስ በመሠረታት የክርስቲያን ጥምቀት አጠመቁ/ተጠመቁ ለማለት ነው እንጂ ሐዋርያት የጌታን ትእዛዝ ጥሰው በወልድ (በክርስቶስ) ስም ብቻ አጥምቀዋል ማለት አይደለም፡፡

# የክርስቲያን ጥምቀት አንዲት ናት

- የክርስቲያን ጥምቀት የማትደገም፣ ለአንድ ሰው አንድ ጊዜ ብቻ የምትሰጥ ናት፡፡
- ጌታችን የተጠመቀው አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ጥምቀት አንድ ጊዜ ብቻ የተከናወነውን የጌታችንን ሞት እና ትንሣኤ የምንሳተፍበት ስለሆነ አይደገምም፡፡
- ‹‹… አንድ ጌታ፣ አንድ ሃይማኖት፣ አንዲት ጥምቀት…›› (ኤፌ 4፣5)፡፡
- ሃይማኖታቸውን የተዉ ክርስቲያኖች ወደሃይማኖታቸው መመለስ ቢፈልጉ ንስሐ እንዲገቡ ይደረጋል እንጂ ለሁለተኛ ጊዜ አይጠመቁም (ክርስትና አይነሱም)፡፡

# የጥምቀት አፈጻጸም

- ጥምቀት በአዲስ ሕይወት እንንመላለስ እና ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ ከክርስቶስ ጋር የምንቀበርበት እና የምንነሳበት ምሥጢር ነው (ሮሜ 6፣4፤ ቆላ 2፣12)።
- በመሆኑም ቤ/ክ በጸሎት በከበረ ውኃ ውስጥ በመዝፈቅ (3 ጊዜ ብቅ ጥልቅ በማድረግ)፣ ወይም ደግሞ በቂ ውኃ በማይገኝበት ዘመን እና ቦታ ውኃውን በተጠማቂው ላይ በማፍሰስ ታጠምቃለች።
- በቤተክረስቲያናችን ማጥመቅ (ምስጢረ ጥምቀትን መፈጸም) የሚችለው ካህን (ቄስ ወይም ጳጳስ) ነው።
- ስለሥርዓቱ ዝርዝር አፈጻጸም (መጽሐፈ ክርስትናን እና ሌሎች መሰል መጻሕፍትን መመልከት ወይም ሥርዓቱ ሲፈጸም በአካል ተገኝቶ ማየት ይቻላል)።

# የሕፃናት ጥምቀት

- አንዳንድ ተከራካሪዎች ‹‹ያመነ የተጠመቀም ይድናል…›› ስለሚል ሕፃናት ማመን እና እምነታቸውን መመስከር ስለማይችሉ መጠመቅ የለባቸውም ብለው ያስተምራሉ (ሌሎች ምክንያቶችንም የሚዘረዝሩ አሉ) ፡፡
- ቤ/ክ ግን ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ እንደ አዋቂዎች ሁሉ ከአማኝ ቤተሰብ የተገኙ ሕፃናትን ታጠምቃለች፡-
  - ሕፃናት ወደኔ ይመጡ ዘንድ ተዉ አትከልክሏቸው፤ እግዚአብሔር መንግሥት እንደነዚህ ላሉት ናት እና›› (ማቴ 19፥14)

# የሕፃናት...

- ማንም ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ (ካልተጠመቀ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት መውረስ አይችልም (ዮሐ 3፣3-6)።
- በሐዋርያት ዘመን በርካታ ሕጻናት ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንደተጠመቁ በተደጋጋሚ ተገልጾአል (ሐዋ 16፣15፤ 16፣33፤ 10፣48፤ 1ቆሮ 1፣15-16...)።
- የተለያዩ የቤ/ክ የታሪክ መጻሕፍትም ሰፊ የታሪክ መረጃዎችን ያቀርባሉ።

# ሕፃናት የሚጠመቁበት ዕድሜ

- በብሉይ ኪዳን ወንዶች ሕፃናት በተወለዱ በ40 ቀናቸው (7+33= 40)፣ ሴቶች ደግሞ በተወለዱ በ80 ቀናቸው (2x7+66= 80) ካህኑ ወዳለበት ወደመገናኛው ድንኳን (ደብተራ ኦሪት/ በኋላ በቤተመቅደስ ተተክቷል) ተወስደው እንዲባረኩ ታዟል (ዘሌ 12፣1-8፤ ኩፋሌ 4፣4-13)።

- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ፈጻሜ ህግ እንደመሆኑ መጠን በተወለደ በአርባ ቀኑ ወደቤተመቅደስ ተወስዷል (ሉቃ 2፣22-28)።

# ሕፃናት የሚጠመቁበት...

- ቤ/ክ ይህንን መሠረት በማድረግ ሕፃናትን በ40 እና በ80 ቀናቸው ታጠምቃለች። ይሁን እና በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከተባሉት ቀኖች ቀድመው ወይም ዘግይተው የሚመጡ ሕፃናትም ይጠመቃሉ።

- ሲጠመቁም ስመ ጥምቀት (የክርስትና ስም) ይወጣላቸዋል። ይህም በብሉይ ኪዳን በግርዘት እለት ይከናወን የነበረውን ስም የመሰየም ሥርዓት የተካ ነው (ሉቃ 1፥13፤ 2፥21)።

# የክርስትና አባት እና እናት

- ቤ/ክ እያንዳንዱ ተጠማቂ በተለይም ሕፃናት ከሥጋ ወላጆቻቸው ሌላ ሃይማኖትን እና ክርስቲያናዊ ስነምግባርን የሚያስተምሩ የክርስትና አባት እና እናት እንዲኖራቸው ታስተምራለች፡፡

- የክርስተና አባት/ እናት መሆን የሚቻለው በጾታ ነው (ለወንድ ወንድ፣ ለሴት ደግሞ ሴት)፡፡ ይህም በጾታቸው እንዲያስተምሯቸው ታስቦ ነው፡፡

- የክርስተና አባት/ እናት ለመሆን ሃማኖትን በሚገባ ማወቅ፣ በስነ ምግባር መታነጽ፣ እና በዕድሜ ብቁ መሆን ያስፈልጋል፡፡

- በመጨረሻም የክርስተና አባት/ እናት የተጠማቂውን ጣት ይዘው በቤ/ክ ፊት የገቡትን ቃል ማክበር/ መጠበቅ እና ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡

# መስብሃት ለእግዚአብሔር!

## በቀጣይ

- ምሥጢረ ቅብዓተ ሜሮን
- ምሥጢረ ቁርባን
- ምሥጢረ ክህነት
- ምሥጢረ ተክሊል
- ምሥጢረ ንስሓ
- ምሥጢረ ቀንዲል